ክፍል ፫

ልሳነ ግእዝ

ሐራተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

ግእዝ
አራተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት
ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ)
የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

ያግኙን

Email
office@eotc-gssu.org
YouTube
https://www.youtube.com/channel/UC83LE1vp0FBsV2TEfcpSmUg
Facebook
http://facebook.com/EOTC.GSSU
Telegram
https://t.me/EOTCNSSU
Website
https://eotc-gssu.org/a/
Twitter
https://twitter.com/tibeb_felege

Copyright ©
2015 E.C

መክስተ አርዕስት

ምዕራፍ አሐዱ

፩.፩ የግእዝ ንባብ አይነቶች..... ፩

፩.፪ መዝሙረ ዳዊት ፩-፫..... ፬

ምዕራፍ ክልኤቱ

፪.፩ የግእዝ የንባብ ስልቶች..... ፰

፪.፪ መዝሙረ ዳዊት ፬-፰.....፲፪

ምዕራፍ ሠለስቱ

፫.፩ አጫጭር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች..... ፲፭

፫.፪ መዝሙረ ዳዊት ፱..... ፲፰

ምዕራፍ አርባዕቱ

፬.፩ የንባብ ክለሣ ..... ፳

፬.፪ መዝሙረ ዳዊት ፲-፲..... ፳

ዋቢ መጻሕፍት

ምዕራፍ አሐዱ
የግእዝ ንባብ አይነቶች



ዓላማ
ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

በቃላቸው ከአአትብ ገጽየ ጀምረው የሳምንት ውዳሴ ማርያም በየቀኑ ያደርሳሉ
.መርሐ ግብራቸውን በግእዝ ጸሎት ይከፍታሉ ይዘጋሉ
.ውዳሴ ማርያምን አውቀው በተጠየቁ ጊዜ ይመልሳሉ
.በማኅበርም ሆነ በግል ውዳሴ ማርያም ያደርሳሉ።
.ምግብ በልተው ስብሐት በግእዝ ያደርሳሉ
.ከቤታቸው ሲወጡ እና ሲተኙ ውዳሴ ማርያም ያደርሳሉ
.አንቀጸ ብርሃንን እና ይዌድስዋን በቃል አጥንተው ውዳሴ ማርያም ያድላሉ ሲታደል ተቀብለው ያደርሳሉ



ተስእሎታተ መራትት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

ሀ) ተማሪዎች ንባብ ማለት ምን ማለት ነው?
ለ) የንባብ ዓይነቶች ስንት ናቸው?

የግእዝ ንባብ

ንባብ፦ “አንበበ፣ አነበበ ” ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን በጽሑፍ የሠፈረን መልእክት ማነብነብ፣መናገር ፣ ሆሄያትን መጥራት፣ መቁጠር፣ወዘተ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡
አለቃ ኪዳነ ወልድም “ንባብ በቁሙ፤ ነገር፣ ቃል፣ ጩኸት” (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ ፮፻፲፱) በማለት ይፈቱታል፡፡ አለቃ ቃል፣ ጩኸት በማለት የገለጹት ድምፅን አውጥቶ የሚያነበንቡትና የሚጠሩት መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ ፡- ንባብ ማለት ከአንድ የተጻፈ ነገር ላይ መሠረታዊ የሆነውን ሐሳብ መረዳት፣ ነጥሎ ማውጣት፣የጸሓፊውን መልእክት መገንዘብ፣ወዘተ እንደሆነ የቋንቋ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ሥርዓተ ንባብ፦ በማንኛውም ቋንቋ የአነባበብ ሥርዓት አለ፡፡ በአነባበብ ሥርዓትም የተነሣ በድምፅም፣ በቃላትም፣ በመዋቅርም ወዘተ ተመሣሣይ ከሆኑ አደረጃጀቶች (መዋቅሮች) የተለያዩ መልእክቶችን እናገኛለን፡፡ የአነባበብ ሥርዓታችንን ባለማስተካከላችን በርካታ የትርጉም ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ ይህ እንደ ማንኛውም ቋንቋ ሲሆን በግእዝ ቋንቋ ደግሞ እጅግ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡

የግእዝ ቋንቋ ሥርዓተ ንባብን ስናነሣ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ልብ ሊባሉ ከሚገቡ ነገሮች መካከል የመጀመሪያው በቁጥር፣ በግእዝ፣ በውርድና በቁም ንባብ የሚነበበው ነው፡፡

ግእዝ ንባብ መሠረታዊ የሆኑ አራት ክፍላት አሉት፡፡ እነርሱም፡

፩.ቁጥር
፪.ግጋዝ (ግእዝ)
፫.ውርድ ንባብ
፬.ቁም ንባብ

ሀ. ቁጥር፡- ቁጥር ማለት የሁሄያቱን (የፊደላቱን) ስያሜ ቅርጽና ድምፅ አንድ በአንድ ወይም በዝርዝር እየቆጠሩ መማር(ማወቅ) ማለት ሲሆን ይከውም አንድ የግእዘዝ ሁሄ(ፊደል) ከግእዝ እስከ ሳብዕ የሚረባ ሰባት ዐይነት የተለያየ ስያሜ፣ ቀርጽ እና ድምፅ አለው፡፡

ለ. ግጋዝ፡- የግእዝ ንባብ ሁለተኛው ክፍለ ትምህርት ነው፡፡ ግጋዝ ማለት አንድን ነገር ተሸግሞ ቀስ በቀስ መጓዝ (መሄድ) ማለት ሲሆን የተለያየ ዐይነት ቅርጽ እና ድምፅ ስያሜና ትርጉም ያላቸውንሆሄያት በማገናኘት እና ቃልን በመመሥረት እንዲሁም የዜማ ስልት ባለው ድምፅ የተመሠረተውን ቃል ተሸክሞ መጓዥ ማለት ነው፡፡

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የግእዝ ቃላት የሚመሠረቱበት በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል እነዚህን የግእዝ ቃላት ለመመሥረት አርት መስፈርታት መሟላት አለባቸው፡፡ እነርሱም-

፩.መቁጠር፡- (አብአ፡ሰብሐ)
፪.መጠቅለል(መዋጥ)፡ (ደብር፣ምድር)
፫.ማጥበቅ፡- (ቀደሰ፣)
፬.ማላላት(ቀተለ) ናቸው፡፡

ሐ. ውርድ ንባብ፡ ይህ የንባብ ዐይነት ሦስተኛው ክፍለ ትምህርት

ነው። ውርድ ንባብ ማለት ከቁም ንባብ ዝቅ ባለ ድምፅ የንባቡን አነሳስና አወዳደቅ የጎዘኔታ ስሜት ባለው ዜማዊ ስልት የንባቡን ዜማ ድምፅ ከመምህራን ቀርቦ መጠየቅ ይፈልጋል። ምክንያቱም ዜማን በጆሮ መስማት እንጂ በዐይን ማየት አይቻልምና ይህም የንባብ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የስቅለትና የቅዳሜ ስዑር ጊዜ ተግባር ላይ ሲውል ይታያል።

መ. ቁም ንባብ፡ ቁም ንባብ ማለት ማንኛውንም የግእዝ መጻሕፍት ሁሉ ከነአነባበብ ጠባዩ በፍጥነትና በቅልጥፍና ማንበብ ማለት ነው ቁም ንባብ የንባብ ትምህርት የመጨረሻው ክፍለ ትምህርት ሲሆን ይህን ትምህርት በሚገባ ተምሮ ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ዜማ ትምህርት ይተላለፋል።(መጋቤ ኅሩያን የማነ ብርሃን ጌታሁን፣ውዳሴ ማርያም ዘኂ ዕለታት፣ ገጽ ፬-፰፩)

መዝሙረ ዳዊት ውርድ እና ቁም ንባብ ከመዝሙር ፩- ፫ ድረስ

መዝሙር፡ ፩

ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥኣን መዝሙር ዘዳዊት ሀሌሉያ።

፩ ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን ወዘኢቆመ ውስተ ፍኖተ ኃጥኣን ወዘኢነበረ ውስተ መንበረ መስተሳልቃን።

፪ ዘዳእሙ ሕገ እግዚአብሔር ሥምረቱ ወዘሕጎ ያነብብ መዕልተ ወሌሊተ።

፫ ወይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኀበ ሙሓዘ ማይ እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ።

፬ ወቁጽላኒ ኢይትነገፍ ወኵሉ ዘገብረ ይፈጽም።

፭ አኮ ከመዝ ኃጥኣንሰ አኮ ከመዝ ዳእሙ ከመመሬት ዘይግሕፍ ነፍስ እምገጸ ምድር።

፮ ወበእንተዝ ኢይትነሥኡ ረሲዓን እምደይን ወኢኃጥኣን ውስተ ምክረ ጻድቃን ።
፯ እስመ የአምር እግዚአብሔር ፍኖቶሙ ለጻድቃን ወፍኖቶሙሰ ለኃጥኣን ትጠፍእ።

መዝሙር: ፪

፩ ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ።
፪ ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስሌሙ ኅብረ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ መሲሑ።
፫ ንበትክ እምኔነ ማእሥሪሆሙ ወንገድፍ እምላዕሌነ አርዑቶሙ።
፬ ዘይነብር ውስተ ሰማይ ይሥሕቆሙ ወእግዚአብሔር ይሳለቅ ላዕሌሆሙ።
፭ ሶበ ይነቦሙ በመዐቱ ወበመዐቱ የሀውኮሙ።
፮ አንሰ ተሠየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ በጽዮን በደብረ መቅደሱ።
፯ ከመ እንግር ትእዛዞ ለእግዚአብሔር እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ እንተ ወአነ ዮም ወለደኩከ።
፰ ሰአል እምነየ እውህበከ አሕዛበ ለርስትከ ወምኵናኒከኒ እስከ አጽናፈ ምድር።
፱ ወትሬዕዮሙ በበትረ ኀጺን ወከመ ንዋየ ለብሓ ትቀጠቅጦሙ።
፲ ወይእዜኒ ነገሥት ለብዉ ወተገሠጹ ኵልክሙ እለ ትኴንንዋ ለምድር።
፲፩ ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሀት ወተሐሠዩ ሎቱ በረዐድ።
፲፪ አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር ወኢትትሐጐሉ እምፍኖተ ጽድቅ፡
፲፫ ሶበ ነደት ፍጡነ መዐቱ፤ ብፁዓን ኵሎሙ እለ ተወከሉ ቦቱ።

መዝሙር፡ ፫

፩ እግዚኦ ሚበዝኑ እለ ይሣቅዩኒ ብዙኃን ቆሙ ላዕሌየ።
፪ ብዙኃን ይቤልዋ ለነፍስየ ኢያድኅነኪ አምላክኪ።
፫ አንተሰ እግዚኦ ምስካይየ አንተ ክብርየ ወመልዕለ ርእስየ።
፬ ቃልየ ኀበ እግዚአብሔር ጸራኅኩ ወሰምዐኒ እምደብረ መቅደሱ።
፭ አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ ወተንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንሥአኒ።
፮ ኢይፈርህ እምአእላፍ አሕዛብ እለ ዐገቱኒ ወቆሙ ላዕሌየ።
፯ ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወአድኅነኒ እስመ አንተ ቀሠፍኮሙ ለኵሉሙ እለ ይፃረሩኒ በከንቱ። ስነኒሆሙ ለኃጥኣን ሰበርከ ።
፰ ዘእግዚአብሔር አድኅኖ ላዕለ ሕዝብከ በረከትከ።

የምዕራፍ ፩ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ) አርድዕት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማን በሉ ርቱዕ ወለእመ ኢኮኑ አማን በሉ ሕስው።

፩) የአነባበብ ሥርዓታችንን ባለማስተካከላችን በርካታ የትርጉም ችግሮች ይፈጠራሉ።

፪) ውርድ ንባብ ማለት ከቁም ንባብ ዝቅ ባለ ድምፅ የንባቡን አነሳስና አወዳደቅ የንዘኄታ ስሜት ባለው ዜማዊ ስልት ማንበብ ነው።

፫) “ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ፡_____”በባዶ ቦታው የሚገባ ቃል “አድኅኖ” የሚለው ነው።

ለ) አርድእት ኅርዩ ርቱእ አውስኦት እምነ ዘተውሕቡ።

፬) ማንኛውም የግእዝ ንባብ በፍጥነትና በቅልጥፍና የሚነበበው በ_____ የንባብ ዓይነት ነው።

ሀ) ቁጥር ንባብ

ለ) የቁም ንባብ

ሐ) የማጋዝ

መ) ውርድ ንባብ

፫) የንባቡን አነሳስና አወዳደቅ የነዘኬታ ስሜት ባለው ዜማዊ ስልት የሚነበብ የንባብ ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ) ውርድ ንባብ

ለ) የማጋዝ

ሐ) የቁም ንባብ

መ) ቁጥር ንባብ

፬) አብአ እና ሰብሐ የሚባሉት ግሶች በየትኛው የምባብ አይነት ይነበባሉ?

ሀ) የማጋዝ ለ) ቁጥር ንባብ

ሐ) ውርድ ንባብ መ)የቁም ንባብ

ሐ) ሀቡ ድልው አውስኦት ለዘይጠልዉ ተስእሎታት፡፡

፩) መሠረታዊ የንባብ ዓይነቶች ስንት ናቸው?

፪) መሠረታዊ የንባብ አይነቶችን ምሳሌ በመስጠት አብራርታችሁ ጻፉ?

ምዕራፍ ክልኤቱ
የግእዝ የንባብ ስልቶች

ተስእሎታተ መራትት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

ሀ) ወዳቂ ንባብ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ) የንባብ ስልቶች ስንት ናቸው?

በአነባበብ ሥርዓትም የተነሣ በድምፅም፣ በቃላትም፣ በመዋቅርም ወዘተ ተመሣሣይ ከሆኑ አደረጃጀቶች (መዋቅሮች) የተለያዩ መልእክቶችን እናገኛለን፡፡ የአነባበብ ሥርዓታችንን ባለማስተካከላችን በርካታ የትርጉም ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ ይህ እንደ ማንኛውም ቋንቋ ሲሆን በግእዝ ቋንቋ ደግሞ እጅግ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡ ለምሳሌ ቀደሳ በተነሽና በወዳቂ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም የተለያየ ነው፡፡ ቀደሳ ወአክበራ እምኵሎን መዋዕል ሲል “ቀደሳ” በአነባበብ ሥርዓቱ ወድቆ ይነበብና ትርጉሙምከዕለታት ሁሉ ለይቶ አከበራት የሚል ይሆናል፡፡ ውእቶን አንስት ቀደሳ ፈጣሪሆን ሲል ደግሞ “ቀደሳ” በአነባበብ ሥርዓቱ ተነሥቶ ይነበብና ትርጉሙም እነዚያ ሴቶች ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ የሚል ይሆናል፡፡

የግእዝ ቋንቋ ንባብን ስናነሣ ከቃላቱ ድምፀት ማለትም መነሣት፣ መጣል፣ ተናቦ ከመነበብ፣ ጠብቆ ከመነበብ፣ ላልቶ ከመነበብ ወዘተ ጋር ተያይዞ የሚታይ ጉዳይ አለ፡፡

ይህን ሥርዓት በተመለከተ ሊቃውንት “የ፱፩ዱ መጻሕፍት ምንባባት ፬

ወገን ናቸው። እነርሱም፡- ተነሽ፣ ተጣይ፣ ሰያፍ ፣ወዳቂ ናቸው። ተነሽ በ፰ ፊደላት ይነገራል፤ ተጣይና ሰያፍ በ፩ በሳድስ ይነገራሉ፤ ወዳቂ በ፯ ፊደላት ይነገራል" በማለት ሁሉም የግእዝ ንባብ በእነዚህ ሥርዓተ ንባብ እንደሚካተት ያስረዳሉ።

ዐበይት ንባባት የሚባሉት አራት ሲሆኑ እነሱም ተነሽ፣ ተጣይ፣ ወዳቂና ሰያፍ ናቸው።

ንኡሳን ንባባት ደግሞ ተናባቢ፣ኢተናባቢ፣ጠብቀው የሚነበቡ፣ላልተው የሚነበቡ፣በጥቅል የሚነበቡ፣ በተናጠል የሚነበቡ ወዘተ ናቸው።

፩ ተነሽ ንባብ

ተነሽ ንባብ የሚባለው እንደ ቁጣ ቃል የሚነገር ተፈላጊውን ቀለም አንስቶ አንዝሮ የሚነበብ ንባብ ነው።ተነስተው የሚነበቡ ቃላትን ለመለየት የሚከተለውን ዘዴ እንጠቀማለን።

ሀ, መድረሻ ቀለም ፦ ተነስተው ሊነበቡ የሚችሉ ቃላት በአምስቱ የሆሄ ስልት የጨረሱ እንደሆነ ብቻ ነው።እነዚህም፦ ግእዝ፣ ካዕብ፣ ሳልስ፣ ራብዕ እና ሳብዕ ናቸው። በእነዚህ ያልደረሰ ቃል ፈጽሞ ሊነሳ አይችልም። ምሳሌ፦ **በግእዝ** ፡ ቆመ፣ ገብረ፣ ሐቀለ፣ አንፈርዐፀ፣ ሰበከ

በካዕብ፡ ቆሙ፣ገብሩ፣ሐቀሉ፣አንፈርዐፁ፣ሰበኩ

በሳልስ፡ ቁሚ፣ግበሪ፣ ሕቅሊ፣ስብኪ፣ቀድሲ

በሳብዕ፡ አሥመረቶ፣ንሴብሖ፣ይግብሮ

በግእዝ ወይም በሌሎቹ የጨረሰ ሁሉ ግን ተነስቶ ይነበባል ማለት አይደለም። ለምሳሌ የሚከተሉትን ህገወጦች መመልከት እንችላለን።
ህየ፣ እወ፣ ሠለስተ፣ ክልዔተ፣ አርባዕተ በግእዝ ቢጨርሱም ተነስተው አይነበቡም። አሐዱ፣ ክልዔቱ፣ ሠለስቱ፣ አርባዕቱ በካዕብ ቢጨርሱም አይነሱም።

ለ, ተነባቢ ቀለም ፦ የተነሽ ቃላት ተነባቢ ቀለማቸው ቅድመ መድረሻቸው ነው። ቅድመ መድረሻቸው ቆጣ ነዘር ብሎ ይነበባሉ።
ምሳሌ፡ አእመረ፣ወረደ፣ቀተለ፣ሐወጸ

ሐ, የቃል ክፍል ፦ በአብዛኛው ተነስተው የሚነበቡ ቃላት ግሶች ናቸው።

ማስታወሻ፦ ሶስት ቀለም ያላቸው በግእዝ ጀምረው ቅድመ መድረሻቸው ሳድስ በሆኑ ግሶች ሳድስ ቀለሙ ተውጦ ይነበባል።
ምሳሌ፦ ገብረ፣ ፈርሐ፣ መርሐ፣ መጽዐ ጎረየ ዐሥርተ ወክልዔተ አርድእተ አቅረብኩ ለከ እሳተ ወማየ ደይ እዴከ ጎበ ዘፈቀድከ ንሴብሐከ እግዚኦ

፪ ተጣይ ንባብ

ተጣይ ቀለማት ሲነበቡ እንደ ወዳቂ ቀለም ያዝ ለቀቅ በማድረግ ነው።
ሀ, መድረሻ ቀለም ፦ ተጣይ ቀላት የሚጨርሱት በሳድስ ቀለም ብቻ ነው።
ምሳሌ፦ ቅዱስ፣ ጎሩይ፣ መንሱት፣ መንበር፣ ሰዋስው፣ ልብ፣ ዮም፣ ጾም

ለ, ተነባቢ ቀለም፦ የተጣይ ቀለም ተነባቢ ቀለሙ ቅድመ መድረሻው ስለሆነ ይህን ቀለም ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባሉ።

ሐ, የቃል ክፍል፦ ተጣይ ቃላት በአብዛኛው ስሞች ናቸው። ከግስ የወጡ ዘሮች በአብዛኛው ተጥለው ይነበባሉ።
ምሳሌ፦ ጎሩያን፣ ቡሩክ፣ ሲሳይ፣ መላእክት ፃድቃን ወሰማዕት ጽኑዓን በሃይማኖት ንጉሥ ወካህናት ክቡራን በጎበ እግዚአብሔር
ማስታወሻ፦ የተጣይ ቃላት ሳድስ ቀለማት ተከታትለው ሲመጡ ቅድመ መድረሻቸው ተውጦ ይነበባሉ።

ምሳሌ፦ ወርቅ፣ ፍቅር፣ ምድር፣ ምግብ፣ ዘርዕ፣ ቅድስት፣ ትስብእት

፫ ወዳቂ ንባብ

ይህ የንባብ ዓይነት ተፈላጊውን ቀለም ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባል፡፡ ወዳቂ ንባብ ወዳቂ ዜማ ባለው ድምጸ ማኅዘኒ ይነበባል፡፡

ሀ, መድረሻ ቀለም፦ የወዳቂ ቀለማት መድረሻ ቀለማት ሰባቱም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፦ **በግእዝ፦** ህየ፣ አሐደ፣ ክልዔተ

በካዕብ፦ ኵሉ፣ ብሒሩ፣ ዝንቱ፣ እሙንቱ፣ እማንቱ

በሳልስ፦ ቀታሊ፣ ገባሪ፣ ዛቲ፣ ኖላዊ፣ ነጋሢ፣ ዜናዊ

በራብዕ፦ ዜና፣ መና፣ ሠረገላ፣ ተድላ፣ መክራ፣ ሀገራ

በኀምስ፦ አይቴ፣ ምናኔ፣ ሥላሴ፣ ልምላሜ፣ ትካዜ

በሳድስ፦ ዝ ብቻ ነው(በሳድስ ወዳቂ ዝ ብቻ ነው)

በሳብዕ፦ ከበሮ፣ አእምሮ፣ እፎ፣ ተዋህዶ

ለ, ተነባቢ ቀለም፦ በወዳቂ ንባብ ጊዜ ተነባቢ ቀለሙ መድረሻ ቀለሙ ነው፡፡ተነባቢ ቀለሙን ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባል፡፡

ሐ, የቃል ክፍል፦ ወድቀው የሚነበቡ በአብዛኛው ስሞች ናቸው፡፡ በዚህ ትምህርት ከግስ ውጭ ያሉትን ሁሉ በስም ስር መድበናቸዋል

፬ ሰያፍ ንባብ

ይህ የንባብ ዓይነት ተፈላጊውን ቀለም እንደ ተነሽ ንባብ አስቆጥቶ አንዝሮ ይነበባል፡፡

ሀ, መድረሻ ቀለም፦ ሰያፍ ንባብ በሳድስ ብቻ ይጨርሳል፡፡

ለ, ተነባቢ ቀለም፦ ተነባቢ ቀለሙ ቅድመ መድረሻው ነው፡፡

ሐ, የቃል ክፍል፦ ተሰይፈው የሚነበቡ ስሞችም ግሶችም ናቸው፡፡

ምሳሌ፦ አእመረት፣ ቀተለት፣ ይወርድ፣ ይገብር፣ እቀትል፣ ቅትል፣

ግበር፣ ንላዕ ኢሳይያስ፣ ቶማስ፣ ገብርኤል፣ ጴጥሮስ፣ ዳንኤል፣ ቴዎፍሎስ ገብርኤል ሰብሐ ኪያሃ ንዑም ፆመ ወናፍቅር ቢጸነ

ማስታወሻ ሰያፍ እና ተነሽ በአነባበብ አንድ ናቸው የሚለያዩት በመድረሻ ቀለማቸው ነው። ወዳቂ እና ተጣይ ሥርዓተ ንባባቸው አንድ ነው ቢባልም በተነባቢ ቀለም እና በመድረሻ ቀለም ይለያያሉ።

መዝሙረ ዳዊት ውርድ እና ቁም ንባብ መዝሙር ፬ እና ፭ ድረስ

መዝሙር፡ ፬

፩ ሶበ፡ ጸዋዕክዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ሰምዐኒ፡ ጽድቅየ፡ ወእምንዳቤየ፡ አርሐበ፡ ሊተ።

፪ ተሥሀለኒ ፡ ወስምዐኒ ፡ ጸሎትየ።

፫ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ፡ ታክብዱ፡ ልብክሙ ፡ለምንት ፡ ታፈቅሩ ፡ ከንቶ፡ ወተኀሡ ፡ ሐሰተ።

፬ አእምሩ፡ ከመ፡ ተሰብሐ፡ እግዚአብሔር፡ በጻድቁ፤ እግዚአብሔር፡ ይሰምዐኒ፡ ሶበ፡ ጸራኅኩ፡ ኀቤሁ።

፭ ተምዑ ፡ ወኢተአብሱ ፤ወዘትሔልዩ፡ በልብክሙ ፡ ውስተ ፡ ምስካቢክሙ፡ ይትዐወቅክሙ።

፮ ሡዑ፡ መሥዋዕተ ፡ ጽድቅ፡ ወተወከሉ፡ ለእግዚአብሔር።

፯ ብዙኃን፡ እለ፡ ይቤሉ፡ መኑ፡ ያርእየነ፡ ሠናይቶ፤ተዐውቀ ፡ በላዕሌነ፡ ብርሃነ፡ ገጽከ ፡ እግዚኦ።

፰ ወወደይከ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ፡ ልብነ እምፍሬ፡ ስርናይ ፡ ወወይን፡ ወቅብእ ፡ በዝኃ።

፱ በሰላም ፡ቦቱ፡ እስክብ፡ ወእነውም።

፲ እስመ ፡ እንተ ፡ እግዚኦ ፡ በተስፋ፡ ባሕቲትከ ፡ አጎደርከኒ።

መዝሙር ፩

፩ ቃልየ ፡ አፅምእ ፡ እግዚኦ ፡ ወለቡ፡ ጽራኅየ ፤
፪ ወአፅምአኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ፤ንጉሥየኒ ፡ ወአምላኪየኒ ።
፫ እስመ ፡ ኀቤከ ፡ እጼሊ ።።እግዚኦ፡ በጽባሕ፡ስምዐኒ ፡ቃልየ ።
፬ በጽባሕ ፡እቀውም፡ ቅድሜከ፡ ወአስተርኢ ፡ ለከ ።
፭ እስመ ፡ ኢኮንከ ፡ አምላከ ፡ ዘዐመፃ ፡ ያፈቅር ፡ወኢየኀድሩ ፡ እኩያን፡ ምስሌከ ።
፮ ወኢይነብሩ፡ ዐማፅያን ፡ ቅድመ፡ አዕይንቲከ ፡ጸላእከ ፡ እግዚኦ፡ ኵሎሙ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ፤ወትገድፎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነቡ ፡ ሐሰተ።
፯ ብእሴ ፡ ደም ፡ ወጕሕላዌ፡ ይስቆርር ፡ እግዚአብሔር ።
፰ ወአንሰ ፡ በብዝኀ ፡ ምሕረትከ፡ እበውእ ፡ ቤተከ ፤ወእሰግድ ፡ ውስተ፡ ጽርሐ ፡ መቅደስከ ፡ በፍሪሆትከ ።
፱ እግዚኦ ፡ ምርሐኒ ፡ በጽድቅከ ፤ወበእንተ፡ ጸላእትየ ፡ አርትዕ ፡ ፍኖትየ፡ ቅድሜከ ። ፲ዐ እስመ ፡ አልቦ፡ ጽድቅ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፤ልቦሙኒ፡ ከንቱ ።
፲፩ ከመ ፡ መቃብር ፡ ክሡት፡ ጕራዒቶሙ ፤ወጸልሃዉ ፡ በልሳናቲሆሙ ።
፲፪ ኰንኖሙ ፡ እግዚኦ ፡ ወይደቁ፡ በውዴቶሙ ፤ወበከመ ፡ ብዝኀ፡ ሕብሎሙ፡ ስድዶሙ ፤እስመ፡ አምረሩከ፡ እግዚኦ ።
፲፫ ወይትፌሥሑ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይትዌከሉከ ፡ለዓለም፡ ይትሐሠዩ ፡ ወተኀድር ፡ ላዕሌሆሙ ።
ወይትሜክሑ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ።
፲፬ እስመ ፡ አንተ ፡ ትባርኮ፡ ለጻድቅ ፤ እግዚኦ ፡ ከመ፡ ወልታ ፡ ሥሙር ፡ከለልከነ።

የምዕራፍ ፪ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ) አርድዕት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማን በሉ ርቱዕ ወለእመ ኢኮኑ አማን በሉ ሕስው።

፩) ወዳቂ የሚባሉት መድረሻቸው ከሳድስ ውጪ የሆኑ ግሶች ናቸው።

፪) "በይነገዝ" በሳድስ ስለጨረሰ ተጣይ ንባብ ነው።

፫) ዐበይት ንባባት የሚባሉት በቁጥር አራት ናቸው።

ለ) አርድእት ጎርዩ ርቱእ አውስኦት እምነ ዘተውሕቡ።

፬) ከሚከተሉት ውስጥ ሰያፍ ንባብ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ይወርድ

ለ) ምድር

ሐ) አሥመረቶ

መ) ቅድስት

፭) ከተሰጡት አማራጮች መካከል ልዩ የሆነውን የቱ ነው?

ሀ) ዳንኤል ለ) አእምሮ

ሐ) ዝ መ) መና

፮) ሰያፍ እና ተነሽ በአነባበብ አንድ ናቸው የሚለያዩት በ_____ነው።

ሀ) ልዩነት የላቸውም ለ) በመድረሻ ቀለማቸው

ሐ) መልስ የለም መ) ሁሉም

፯) "ፍቅር" _____ንባብ ነው።

ሀ) ሰያፍ ለ) ወዳቂ

ሐ) ተጣይ መ) ተነሽ

ሐ) ሀቡ ድልው አውስኦት ለዘይጠልዉ ተስእሎታት።

፩) የንባብ ስልቶች የሚባሉት ስንት ናቸው? በዝርዝር አስቀምጧቸው።

፪) በሰያፍ እና በተጣይ ንባባት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ምንድር ነው?

ምዕራፍ ሠለስቱ
አጫጭር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች

ተስእሎታተ መራትት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከዚህ ቀደም ባላችሁ እውቀት ተመርኩዛችሁ መልስ ስጡባቸው፡፡

፩. ተማሪዎች ስለ ይሥሐቅ ታሪክ የምታቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

፪. “ወፈነዎ ለሳሙኤል ነቢይ ከመ ይቅብዖ ቅብዐ መንግሥት” የሚለውን ዓረፍተ ነገር የንባ ስልቶቹን ለይጣችሁ አስቀምጡ፡፡

፫.፩ በእንተ በረከተ ተአዝዞት

ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ መዋዕል አምኀሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይብሎ አብርሃም አብርሃም ወይቤ ነየ አነ ። ወይቤሎ ንሥእ ለዋልድከ ዘታፈቅር ይስሐቅ ወሑር ውስተ ደብር ላዕላይ ወአዕርጎ ህየ ወሡዖ ላዕለ አሐዱ ደብር ዘእቤለከ። ወተንሥአ አብርሃም በጽባሕ ወረሐነ አድኅ ወነሥአ ፪ ደቆ ወይስሐቅሂኒ ወልደ ወሠጸረ ዕፅወ ለመሥዋዕት ወአጸረ ወሖረ ወበጽሐ ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ይቤሎ እግዚአብሔር በሣልስት ዕለት፡፡

ወነጸረ አብርሃም በአዕይንቲሁ ወርእየ መካነ እምርሑቅ ወይቤሎሙ አብርሃም ለደቁ ንብረ ዝየ ምስለ አድግ አነ ወወልድየ ነሐውር እስከ ደብር ወሰጊደነ ንገብእ ኀቤክሙ ዝየ ። ወነሥአ አብርሃም ዕፀወ ዘመሥዋዕት ወአጸሮ ለይስሐቅ ወልዱ ወነሥአ እሳተኒ ውስተ እዴሁ ወመጥባሕተኒ

ወሖሩ ክልኤሆሙ ኀቡረ። ወይቤሎ ይስሐቅ ለአብርሃም አቡሁ አባ ወይቤሎ ምንት ውእቱ ወልድየ ወይቤሎ ናሁ ዕፅ ወእሳትኒ አይቴ ሀሎ በግዑ ለመሥዋዕት ። ወይቤሎ አብርሃም እግዚአብሔር ይሬኢ ሎቱ በግየ ለመሥዋዕት ወልድየ ወሖሩ ኀቡረ ። ወበጽሑ ውስተ ውእቱ መካን ዘይቤሎ እግዚአብሔር ወነደቀ አብርሃም ምሥዋዕ መልዕልተ ዕፀው ። ወአልዐለ እዴሁ አብርሃም ከመ ይንሣእ መጥባሕተ ወይሕርዶ ለወልዱ። ወጸውዖ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይቤሎ አብርሃም አብርሃም ወይቤ ነየ አነ ። ወይቤሎ ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ ወኢትግብር ቦቱ ምንተኒ ይእዜ አእመርኩ ከመ አንተ ትፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢመሀኮ እምኔየ ለወልድከ ዘታፈቅር ። ወሰበ ነጸረ አብርሃም ርእየ ናሁ አሐዱ በግዕ ወእጉዝ አቅርንቲሁ በዕፅ ሳቤቅ ወሖረ አብርሃም ወነሥአ ወሥየ ህየንተ ይስሐቅ ወልዱ

፫.፮ ጥበበ እግዚአብሔር በልደተ ሙሴ

ወሀሎ ፩ ብእሲ እምነገደ ሌዊ ዘስሙ እንበረም ዘነሥአ ሎቱ እምአዋልደ ሌዊ ብእሲተ።ወፀንሰት ወወለደት ተባዕተ ወሶበ ርእይዎ ከመ ሠናይ ውእቱ አንበርዎ ፫ አውራኀ። ወሶበ ስእኑ እንከ ኀቢኦቶ ነሥአት እሙ ነፍቀ ወቀብዐተ አስፈሊጣ ወፒሳ ወወደየቶ ለውእቱ ሕፃን ውስቴታ ወሜመቶ ውስተ ማዕዶት ኀበ ገበዘ ተከዚ። ወትሐውድ እኅቱ እምርኁቅ ከመ ታእምር ምንት ይበጽሖ። ወወረደት ወለተ ፈርዖን ትትኀፀብ በውስተ ተከዚ ወአንሶሰዋ አዋልዲሃ ኀበ ተከዚ ወሶበ ርእየትታ ለይእቲ ነፍቅ ውስተ ማእዶት ፈነወት ወለታ ወአምጽኦታ። ወከሠተታ ወርእየት ሕፃነ ይበኪ ውስተ ይእቲ ነፍቅ ወምህከቶ ወለተ ፈርዖን ወትቤ እምደቂቀ ዕብራውያት ውእቱ ዝ ሕፃን። ወትቤላ እኅቱ ለውእቱ ሕፃን ለወለተ ፈርዖን ትፈቅዲኑ እጸውዕ ለኪ ብእሲተ ሐፃኒተ ዕብራዊተ ወትሕፅኖ ለዝ ሕፃን። ወትቤላ ወለተ ፈርዖን ዕቀቢ ሊተ ዘ ሕፃነ ወሕፅኒዩ ወአነ እሁበኪ ዐስበኪ ወነሥአቶ ይእቲ ብእሲት ለውእቱ ሕፃን ወሐፀነቶ። ወሶበ ጸንዐ ውእቱ ሕፃን ወሰደቶ ኀበ ወለተ ፈርዖን ወኮና ወልደ ወሰመየቶ ስሞ

ሙሴ ወትቤ እስመ እማይ አውጽእክሆ።

፫.፫ በእንተ ኃይለ ዝማሬ

ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘስሙ ዳዊት ወውእቱ ንጉሠ እስራኤል እስመ እምቅድሜሁ ለእግዚአብሔር ዘሖረ ሐረተ ሠናየ ወገብረ ፍትሐ ወጽድቀ እምኵሎሙ ነገሥተ እስራኤል ወውእቱ እምነገደ ይሁዳ ዘእምቤተልሔም ወነረዮ እግዚአብሔር ከመ ይኩን ንጉሠ ለእስራኤል ሶበ ተዐደወ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ሳኦል። ወፈነዎ ለሳሙኤል ነቢይ ከመ ይቅብዖ ቅብዐ መንግሥት ወነረዮ ሳሙኤል ለወልደ እሴይ ወርእየ ዘይልሕቅ እስመ ሠናይ አርአያሁ ወጽኑዕ ሥጋሁ ወኢነረዮ እግዚአብሔር አላ ይቤሎ ኢትርአይ ገጸ ወኢትነጽር ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ እስመ አኮ ዘከመ ይሬኢ ሰብእ ዘይሬኢ እግዚአብሔር እስመ ሰብእ ገጸ ይሬኢ ወእግዚአብሔር ልበ ይሬኢ።

ወእምድኅረ ሰብዓቲሆሙ ደቂቁ ለእሴይ ቀብዖ ለዳዊት ሳሙኤል ነቢይ ይንግሥ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ወኮነ እግዚአብሔር ምስሌሁ በኵሉ ግብሩ። ወነደኅ መንፈሰ እግዚአብሔር ለሳዖል ወሐነቆ መንፈስ እኩይ እም እግዚአብሔር። ወይቤልዎ ደቁ ለሳዖል ናሁ መንፈስ እኩይ የሐንቀከ እምኀበ እግዚአብሔር ይንግሩ አግብርቲከ ቅድሜከ ወይሕየው እግዚኦሙ ወንጎሥሥ ለከ ብእሴ ዘይዜመር በመሰንቆ ወእምከመ ወጽአ ላዕሌከ ዝንቱ መንፈስ እኩይ ይዜምር ውእቱ በመሰንቆ ወተሐዩ አንተ ወያዐርፈከ። ወይቤሎሙ ሳኦል ለደቁ ርእዩ ሊተ ብእሴ ሠናየ ዜምር ወአምጽእዎ ሊተ። ወአውሥአ ፩ እም ደቁ ወይቤ ርኢክዎ ለወልደ እሴይ ዘቤተልሔም እንዘ ይዜምር ወጠቢብ ብእሲሁ ወመስተቃትል ውእቱ ወለባዊ በቃሉ ወሠናይ ራእዩ ወእግዚአብሔር ምስሌሁ ። ወለአከ ሳኦል ሐዋርያተ ኀበ እሴይ እንዘ ይብል ፈንዎአ ሊተአ ለወልድከአ ዳዊትአ ዘውስተ መራዕዩከአ ። ወነሥአ እሴይ መሥነቅተ ኀብስት ወዝቀ ወይነ ወጸዐነ ዲበ አድግ ወፀ ማሕስዐ ጠሊ ወፈነወ ምስለ ዳዊት ወልዱ ኀበ

ሳኦል። ወቦአ ዳዊት ኀበ ሳኦል ወቆመ ቅድሜሁ ወአፍቀሮ ጥቀ ወረሰዮ ሎቱ ዘይጸውር ንዋየ ሐቅሉ። ወለአከ ሳኦል ኀበ እሴይ እንዘ ይብል ለይንበርአ ዳዊትአ ኀቤየአ ወይቁምአ ቅድሜየአ እስመ ረከበ ሞገሰአ ቅድመ አዕይንትየአ ። ወእምዝ ሶበ ይመጽእ ዝክቱ መንፈስ እኩይ ላዕለ ሳኦል ይነሥእ ዳዊት መሰንቆሁ ወይዜምር በቅድሜሁ ወየዐርፍ ሳኦል ወይኤድም ወየኀድኅ መንፈስ ርኩስ።

መዝሙረ ዳዊት ውርድ እና ቁም ንባብ መዝሙር ፮

መዝሙር፡ ፮

፩ እግዚኦ፡ በመዐትከ፡ ኢትቅሥፈኒ፤ ወበመቅሠፍትከ፡ ኢትገሥጸኒ።

፪ ትሣሀለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ፡ ድውይ ፡ አነ ፤ወፈውሰኒ ፡ እስመ፡ ተሀውኅ ፡ አዕጽምትየ።

፫ ወነፍስየኒ ፡ ተሀውከት፡ ፈድፋደ ፤ ወአንተኒ፡ እግዚኦ ፡ እስከ፡ ማእዜኑ ።

፬ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ ወባልሐ፡ ለነፍስየ፤ወአድኅነኒ ፡ በእንተ ፡ ምሕረትከ ።

፭ እስመ ፡ አልቦ ፡ በውስተ፡ ሞት፡ ዘይዘከረከ ፤ወበሲኦልኒ ፡ መኑ፡ የአምነከ ።

፮ ሰራሕኩ፡ በምንዳቤየ ፡ወአኀፅብ፡ ኵሎ፡ ሌሊተ፡ ዐራትየ ፤ወበአንብዕየ ፡ አርሐስኩ፡ ምስካብየ ።

፯ ወተሀውከት፡ እመዐት፡ ዐይንየ፤ ወበለይኩ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ፡ ጸላእትየ።

፰ ረሐቁ፡ እምኔየ ፡ ኵልክሙ ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ፤እስመ ፡ ሰምዐኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ብካይየ ።

፱ ወሰምዐኒ ፡እግዚአብሔር፡ ስእለትየ፤ ወተወክፈ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሎትየ።

፲ ለይትኀፈሩ ፡ ወይኅሰሩ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ፤ለይገብኡ፡

ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወፍጡነ ።።

የምዕራፍ ፫ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ) አርድዕት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማን በሉ ርቱዕ ወለእመ ኢኮኑ አማን በሉ ሕስው።።

፩) አብርሃም ወደ ሞሪያም ይዞ የወጣው ሁለቱን ልጆቹን ነው።።

፪) ቅዱስ ዳዊት የተመረጠው ከእረኝነት ነው።።

፫) ሙሴ ወደ ፈርኦን ቤት ያስገባቸው እናቱ ናት።።

ለ) አርድእት ኅርዩ ርቱእ አውስኦት እምነ ዘተውሕቡ።።

፩) ከውሃ የተገኘና እስራኤልን ነፃ ያወጣ ማነው?

ሀ) ዳዊት ለ) አብርሃም

ሐ) ሙሴ መ) ይስሐቅ

፪) አብርሃም ይስሐቅን ሊሠዋው ሲል ያገኘውና በይስሐቅ ፈንታ የሰዋው ምንድነው?

ሀ) ሁለተኛ ልጁን

ለ) በዕፀ ሳቤቅ የጠያዘ በግ

ሐ) ሎሌውን

መ) ሁሉም

፫) ከሚከተሉት ስሞች ተጣይ ንባብ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አብርሃም ለ) ይስሐቅ

ሐ) ዳዊት መ) ሙሴ

ሐ) ሀቡ ድልው አውስኦት ለዘይጠልዉ ተስእሎታት።።

፩) ከዳዊት ታሪክ ምን ተማራችሁ?

፪) ከይስሐቅ ታሪክ የተማራችሁትን በዝርዝር ጻፉ።።

ምዕራፍ አርባዕቱ
የንባብ ክለሣ

ኮስእሎታተ መራትት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከዚህ ቀደም ባላችሁ እውቀት ተመርኩዛችሁ መልስ ስጡባቸው።

ሀ. የግእዝ የንባብ ሽልጽ ከሌሎች ቋንቋዎች አንጻር በምን ይለያል?

ለ. በግእዝ የንባብ ስልቶች እና የንባብ አይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

፬.፩ መዝሙረ ዳዊት ውርድ እና ቁም ንባብ ከመዝሙር ፯-፲

መዝሙር፡ ፯

፩ እግዚኦ፡ አምላክየ ፡ ብከ ፡ ተወከልኩ ፡ ወኢትግድፈኒ ፤ወአድኅነኒ ፡ እምኵሉሙ ፡ እለ ፡ ሮዱኒ ፡ ወባልሐኒ።

፪ ከመ ፡ ኢይምስጥዋ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ለነፍስየ ፤እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያድኅን ፡ ወዘይባልሕ ።

፫ እግዚኦ ፡ አምላክየ ፡ እመሰ ፡ ከመዝ ፡ ገበርኩ ፤ወእመኒ ቦ ፡ ዐመፃ ፡ ውስተ ፡ እደውየ ።

፬ ወእመኒ ፡ ፈደይክዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈድዩኒ ፡ እኩየ ፤ለያውድቁኒ ፡ ጸላእትየ ፡ ዕራቅየ ።

፭ ወይዴግና ፡ ፀራዊ ፡ ለነፍስየ ፡ ወይርከባ ፤ወይኪዳ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለሕይወትየ

። ወያኅስሮ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ለክብርየ ።

፮ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ በመዐትከ ፤ወተለዐል፡ መልዕልቶሙ

፡ ለጸላእትየ ።።
፮ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላክየ ፡በሥርዐት ፡ዘአዘዝከ ።። ወማኅበረ ፡ አሕዛብ ፡ የዐውደከ
፯ ወበእንተዝ ፡ ተመየጥ ፡ ውስተ ፡ አርያም።። እግዚአብሔር ፡ ይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ።።
፰ ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ በከመ ፡ ጽድቅከ ፤ወይኩንኒ ፡ በከመ ፡ የዋሃትየ ።።
፱ የኀልቅ ፡ እከዮሙ ፡ ለኃጥኣን ፤ ወታረትዖሙ ፡ ለጻድቃን ፤ይፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ እግዚአብሔር።።
፲ አማን፡ ይረድአኒ ፡ እግዚአብሔር ፤ ዘያድኅኖሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ።።
፲፩ እግዚአብሔር ፡ መኰንነ ፡ ጽድቅ ፡ ኀያል ፡ ወመስተዐግስ ፤ወኢያምጽእ ፡ መንሱተ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ።።
፲፪ እመሰ ፡ ኢተመየጥክሙ፡ ሰይፎ፡ ይመልኅ ፤ቀስቶኒ ፡ ወተረ ፡ ወአስተዳለወ።።
፲፫ ወአስተዳለወ ፡ ቦቱ ፡ ሕምዘ ፡ ዘይቀትል ፤ወአሕጻሁኒ ፡ ለእለ ፡ ይነዱ ፡ ገብረ ።።
፲፬ ናሁ ፡ ሐመ ፡ ዐማፂ ፤ፀንሰ ፡ በጻዕር ፡ ወወለደ ፡ ኃጢአተ
፲፭ ግበ ፡ ከረየ ፡ ወደሐየ ፤ወይወድቅ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ዘገብረ
፲፮ ወይገብእ ፡ ጻማሁ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፤ ወትወርድ ፡ ዐመፃሁ ፡ ዲበ ፡ ድማሉ ።።
፲፯ እገኒ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ጽድቁ ፤ወእዜምር ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ።።

መዝሙር፡ ፰

፩ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስምክ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ፤
፪ እስመ ፡ ተለዐለ ፡ እበየ፡ ስብሓቲከ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት

፫ እምአፈ፡ ደቂቅ፡ ወሕፃናት፡ አስተዳሎከ፡ ስብሐተ፡ በእንተ ፡ ጸላኢ ።ከመ ትንሥዖ፡ ለጸላኢ፡ ወለገፋዒ።።
፬ እስመ ፡ ንሬኢ ፡ ሰማያተ ፡ ግብረ ፡ አጻብዒከ ።
ወርኀ ፡ ወከዋክብተ ፡ ዘለሊከ ፡ ሳረርከ።።
፭ ምንትኑ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ፡ ከመ፡ ትዝክሮ ።ወምንትኑ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ተሐውጾ።።
፮ ሕቀ ፡ አሕጸጽኮ ፡ እምላእክቲከ ።ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ከለልኮ ።።ወሜጎምኮ ፡ ዲበ ፡ኵሉ ፡ ግብረ ፡ እደዊከ ።
፯ ወኵሎ ፡ አግረርከ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ።። አባግዐኒ ፡ ወኵሎ ፡ አልህምተ ። ወዓዲ ፡ እንስሳ ፡ ዘገዳም ።።
፰ አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ፡ወዐሣተ፡ባሕር ።ወዘኒ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍናተ ፡ ባሕር ።።
፱ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስምከ ፡ በኵሉ ፡ ምድር።።

መዝሙር፡ ፱

፩ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ። ወእነግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሓቲከ ።።
፪ እትፌሣሕ ፡ ወእትሐሠይ፡ብከ ወእዜምር፡ ለስምከ ፡ ልዑል
፫ ሶበ ፡ ገብኡ ፡ ጸላእትየ ፡ ድኅሬሆሙ ። ይድወዩ ፡
ወይትሐጐሉ ፡ እምቅድመ ፡ገጽከ ።።
፬ እስመ ፡ ገበርከ ፡ ሊተ ፡ ፍትሕየ ፡ ወበቀልየ ።ወነበርከ ፡ ዲበ ፡ መንበርከ ፡ መኰንነ ፡ ጽድቅ ።።
፭ ገሠጽኮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወተሐጕሉ ፡ ረሲዓን ።ወደምሰስከ ፡ ስሞሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።።
፮ ፀርሰ፡ ተገምሩ፡ በኵናት፡ ለዝሉፍ።። ወአህጉሪሆሙኒ፡ ነሥትከ
፯ ወትስዕር፡ ዝክሮሙ፡ ኀቡረ።። ወእግዚአብሔርሰ፡ ይነብር፡ ለዓለም ።
፰ ወአስትዳለወ ፡ መንበሮ ፡ ለኰንኖ ።። ወውእቱ ፡ ይኴንና ፡

ለዓለም ፡ በጽድቅ ፤ ወይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።
፱ ወኮኖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስካዮሙ ፡ ለነዳያን ወረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤሆሙ ።
፩፰ ወይትዌከሉ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ፤እስመ ፡ ኢተኀድጎሙ ፡ ለእለ ፡ የኀሡከ ፡ እግዚኦ ።
፲፭ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ፤ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።
፲፪ እስመ፡ተዘክረ ፡ ዘይትኃሠሥ ፡ ደሞሙ፤ ወኢረስዐ ፡ ዐውያቶሙ ፡ ለነዳያን ።
፲፫ ተሣሀለኒ፡ እግዚኦ፡ ወርኢ፡ ዘከመ ፡ ያሐመኒ ፡ ጸላእትየ ፤
፲፬ ዘያሌዕለኒ ፡ እምአናቅጸ ፡ ሞት ።
ከመ ፡ እንግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሓቲሁ ፤ በአናቅጺሃ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ፤
፲፭ ወንትፈሣሕ፡ በአድኅኖትከ። ጠግዑ፡ አሕዛብ፡ በጌጋዮሙ ፡ ዘገብሩ ፤
፲፮ ወበይእቲ፡ መሥገርት፡ እንተ፡ ኀብኡ፡ ተሠግረ፡ እግሮሙ
፲፯ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ገቢረ ፡ ፍትሕ
፤ወበግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ተሠግረ ፡ ኃጥእ ።
፲፰ ይግብኡ ፡ ኃጥኣን ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፤ ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ይረስዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፲፱ እስመ ፡ አኮ ፡ ለዝሉፋ ፡ ዘይትረሳዕ ፡ ነዳይ ፤ወኢያሕጕሉ ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ ነዳያን ፡ ለዓለም ።
፳፩ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢይጽናዕ ፡ እጓለ
፡ እምሕያው ፤ወይትኰነኑ ፡ አሕዛብ ፡ በቅድሜከ ።
፳፪ ሢም ፡ እግዚኦ ፡ መምህረ ፡ ሕግ ፡ ላዕሌሆሙ ፤ወያእምሩ ፡ አሕዛብ ፡ ከመ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እሙንቱ ።
፳፫ ለምንት ፡ እግዚኦ ፡ ቆምከ ፡ እምርሑቅ
፤ወትትዔወር ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤ ።

፳፫ በትዕቢቱ ፡ ለኃጥእ ፡ ይውዒ ፡ ነዳይ ። ወይሠገሩ ፡ በውዴቶሙ ፡ እንተ ፡ ሐለዩ

፳፬ እስመ ፡ ይትዌደስ ፡ ኃጥእ ፡ በፍትወተ ነፍሱ ።ወዐማሚኒ ፡ ይትባረክ ፡

፳፭ ወሐኮ ፡ ኃጥእ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወኢተኃሥሦ ፡ በከመ ፡ ብዝኀ ፡ መዐቱ

፳፮ ወአልቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድሜሁ ። ወርኩስ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዊሁ ፡

፳፯ ወንሡት ፡ ኵነኔከ ፡ በቅድሜሁ ። ወይቀንዮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ጸላእቱ።

፳፰ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ኢይትሀወክ ። ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ወኢይርክበኒ ፡እኩይ።

፳፱ ምሉእ ፡ አፉሁ ፡ መርገመ ፡ ወጽልሑተ ።ታሕተ ፡ ልሳኑ ፡ ጻማ ፡ ወሕማም ።

፴ ይጸንሕ ፡ ወይንዑ ፡ ምስለ ፡ ብዑላን ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ ለንጹሕ ፡ በጽሚት ።

፴፩ ወአዕይንቲሁኒ ፡ ኀበ ፡ ነዳይ ያስተሐይጻ።ይጸንሕ ፡ ወይትነባእ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡

፴፪ ይጸንሕ ፡ ከመ ፡ ይምስጦ ፡ ለነዳይ ። ይመስጦ ፡ ለነዳይ ፡ ወይስሕቦ ፡

፴፫ ወያኀስሮ ፡ በመሥገርቱ ።ይትቀጻዕ ፡ ወይወድቅ ፡ ሶበ ፡ ቀነዮ ፡ ለነዳይ ።

፴፬ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ይረስዐኒ ፡ እግዚአብሔር ።ወሜጠ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ ።

፴፭ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላክየ ፡ ወትትለዐል ፡ እዴከ ።ወኢትርስዖሙ ፡ ለነዳያን ።

፴፮ በእንተ ፡ ምንት ፡ አምዕየ ፡ ኃጥእ ፡ ለእግዚአብሔር ።እስመ ፡ ይብል ፡ በልቡ ፡ ኢይትኃሠሠኒ ።

፴፯ ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ለሊከ ፡ ትኔጽር ፡ ጻማ ፡ ወመዐተ ፤ወከመ ፡ ትሜጥዎ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፤
፴፰ ላዕሌከኑ ፡ እንከ ፡ ተገድፈ ፡ ነዳይ ፤ ወአንተኑ ፡ ረዳኢሁ ፡ ለእንለ ፡ ማውታ።።
፴፱ ቀጥቅጥ ፡ መዝራዕቶ ፡ ለኃጥእ ፡ ወለእኩይ ፤ወትትነሠሥ ፡ ኀጢአቱ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወኢትትረከብ ።።
፵ ይነግሥ፡ እግዚአብሔር፡ ለዓለመ፡ ዓለመ ፡ወይትሐኰሉ ፡ አሕዛብ ፡ እምድር ።።
፵፩ ፍትወቶሙ ፡ ለነዳያን ፡ ሰምዐ ፡ እግዚአብሔር ፤ወሕሊና ፡ ልቦሙኒ ፡ አፅምአት ፡ እዝኑ ።።
፵፪ ፍትሑ ፡ ለነዳይ ፡ ወለእንለ ፡ ማውታ ፤ ከመ ፡ ኢይድግሙ ፡ እንከ ፡ እንለ ፡
እምሕያው ፡ አፅብዮ ፡ አፉሆሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።።

መዝሙር፡ ፲

፩ በእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ እፎ ፡ ትብልዋ ፡ ለነፍስየ ፤አዐይል ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ከመ ፡ ዖፍ ።።
፪ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኃጥኣን ፡ ወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ፡
ወአስተዳለው ፡ አሕጻቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምጕንጻቶሆሙ ፤ከመ ፡ ይንድፍዎሙ ፡ ለርቱዕ ፡ ልብ ፡ በጽሚት ።።
፫ እስመ ፡ ናሁ ፡ ዘአንተ ፡ ሠራዕከ ፡ እሙንቱ ፡ ነሥቱ ፤ወጻድቅሰ ፡ ምንተ ፡ ገብረ ።።
፬ እግዚአብሔር፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅድሱ ፡እግዚአብሔር፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ መንብሩ ፤
፭ ወአዕይንቲሁኒ ፡ ኀበ ፡ ነዳይ ፡ ይኔጽራ ፡ ወቀራንብቲሁኒ ፡ የሐቶ ፡ ለእንለ ፡እመሕያው ።።
፮ እግዚአብሔር፡ የሐትቶ ፡ ለጻድቅ ፡ ወለኃጥእ ፤ዘሰ ፡ አፍቀራ ፡ ለዐመፃ ፡ ጸልአ፡ ነፍሶ ።።

፮ ይዘንም ፡ መሣግር ፡ ላዕለ ፡ ኃጥኣን ፤ እሳት ፡ ወተይ ፡ መንፈስ ፡ ዐውሎ ፡መክፈልተ ፡ ጽዋየሙ ።።
፯ እስመ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽድቀ፡ አፍቀረ ፤ወለርትዕሰ ፡ ትሬእዮ ፡ ገጸ ።።

የምዕራፍ ፬ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ) አርድዕት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማን በሉ ርቱዕ ወለእመ ኢኮኑ አማን በሉ ሕስው።።

፩) ቃላትን እየቆጠርን የምናነበው ንባብ ውርድ ንባብ ይባላል።።

፪) ግእዝ ፲ ዓይነት የንባብ አይነቶች አሉት።።

፫) የመጀመሪያው የንባብ ዓይነት ቁም ንባብ ይባላል።።

ለ) አርድእት ኀርዩ ርቱእ አውስኦት እምነ ዘተውህቡ።።

፩) በአማርኛ እንደ ቁጣ ቃል መድረሻ ቀለሙን ይዘን የምናሳይ የንባብ ስልት_____ነው።።

ሀ) ሰያፍ ለ) ወዳቂ

ሐ) ተጣይ መ) ተነሽ

፪) መድረሻ ቀለማቸው ሳድስ ፊደል የሆነ የሚነሣ የንባብ ስልት ዓይነት_____ነው።።

ሀ) ተነሽ ለ) ተጣይ

ሐ) ሰያፍ መ) ወዳቂ

፫) ፀርሰ ተገምሩ በኩናት ለዝሉፍ።። _____ ነሥትከ፤በባዶ ቦታ የሚገባው

ሀ) ወአስተዳለው ለ) ወአህጉሪሆሙኒ

ሐ) ፍትወቶሙ መ) መዝራዕቶ

፬) መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ፲ ምን ብሎ ይጀምራል?

ሀ) እግዚኦ እግዚእነ

ለ) እግዚኦ አምላክየ

ሐ) እገኒ ለከ

መ) በእግዚአብሔር

ሐ) አስተዛምዱ ቃላት ዘሀለዉ በፀጋም ምስለ ቃላት ዘየማን፡፡

ሀ	ለ
፩) ውርድ ንባብ	ሀ. ዳዊትን የቀባ
፪) ግእዝ ንባብ	ለ. መድረሻ ፊደሉን ያዝ አድርገን ጥለን የምናነበው
፫) ወዳቂ ንባብ	ሐ. በሰሙነ ሕማማት የሚነበብ የንባብ አይነት
፬) ሳኦል	መ. ከዳዊት በፊት የነበረ ንጉሥ
፭) ሳሙኤል	ሠ. የመጀመሪያው የንባብ አይነት

ዋቢ መጻሕፍት

፩.መዝሙረ ዳዊት

፪.መጽሐፈ ስንክሳር

ክፍል ፩

ልሳነ ግእዝ

ኮራተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ